Print

mesfinwoldemariam.org

ብዘመነ ግርምቢ.ጥ ማይ ነዓቅብ

የትግርኛው አባባል በዘመነ ተገላቢጦሽ ዝናብ ሽቅብ ይዘንባል ማለት ነው፡፡ በዘመናችን ከሁለት የተለያዩ አቅጣጫዎች በትግራይ ተወላጆች ኢትዮጵያዊነት ላይ የሚሰነዘረው የመለየቱ ጥላሸትና የጥርጣሬ ጥላቻ ብዙ ግዜ የተናገርሁበትና የፃፍሁበት ቢሆንም ችግሩ አሁንም በይፋ ውይይት ያልተደረገበት በመሆኑ አልጠፋም፡፡ በጉዳዩ ላይ በግልፅና በይፋ እንዳንወያይበት የባህላችን ይሉኝታ፡ ማድበስበስና መሸፋፈን ባንድ በኩል፡ በሌላ በኩል አገዛዙ ከእውነት ጋር የተጣላና ቅራኔን በድብብቆሽ የማስፋፋት ፍላጎት ያለው መሆኑ ችግሩን እያባባሰው ነው፡፡

ዛሬ ከትግራይ ጫካ የወጡ እንክርዳዶች በአንድ በኩል ትግሬነት ከኢትዮጵያዊነት፡ በሌላ በኩል ለትግራይ ተወላጆች ተቆርቋሪ በመምሰል ትግሬዎችን ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር በቅራኔ ለማጋጠም መብቃታቸው እኩይ የሆነ የፖለቲካ ውዥንብር ነው፡፡ የቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ በዚህ ውዥንብር ተጠምዶ ከትግራይ ተወላጆች ጋር ያለውን የደም፡ የታሪክ ፡ የባሕል፡ ዜግነት አንድነቱን ያላላል ብዬ አላምንም፡፡  ቀደም ሲልም ኮሎኔል መንግስቱ ሐይለማርያም ለትግራይ ሕዝብ ያለውን ንቀት በግልፅ ለመጠንሰስ በጣም ፈልጎት የነበረው ቅራኔ በኢትዮጵያ ሕዝብ እንደከሸፈ እናውቃለን።

ትግሬዎች ከማንም የበለጠ እንጂ ያላነሰ የኢትዮጵያዊነት መሠረት ናቸው፡፡ ትግሬዎች ለኢትዮጵያ ህልውናና ነፃነት ከማንም የበለጠ እንጂ ያላነሰ መስዋዕትነት ከፍለዋል፡ ትግሬዎች ለኢትዮጵያ የክብር ታሪክ ከማንም የበለጠ እንጂ ያላነሰ አስተዋፅኦ አድርገዋል፡ በምንም መስፈርት ቢሆን የትግሬዎችን የጎላ የዜግነት ድርሻ ቀንሶ ለማውሳት የሚያስችል አይደለም። በአስቸጋሪ ሁኔታ ሆነውም ቢሆን ኢትዮጵያዊነታቸውን ለማወጅ የሚያሳዩት ሁሉ የሚደንቅ ነው። ለምሳሌ ወያኔ በሥልጣኑ ላይ በወጣባቸው በመጀምሪያዎቹ ዓመታት አንድ የኔ ተማሪ የነበረ ወጣት ወደ ውጭ አገር ሄዶ ምህርቱን የመቀጠል ዕድል አገኘ። ስለዚህም ወደትግራይ ሄጄ ዘመዶቼን ሁሉ ለመሰናበት መሄዴ ነውና ለአንድ ወር ያህል አላገኘህምና ሳልሰናበትህ የሄድኩ እንዳይመስልህ ብሎኝ ተለያየን። በአንድ ሳምንት ተመልሶ መጣ። ከሁሉ በፊት የዘመዶቹ የሂድልን ውትወታ ጠንካራ ሆነበት። ዕድሉ ይሰናከልበታል ብለው በጣም ፈርተው ነበር፡ በተጨማሪም የወያኔ ካድሬዎች በየሄደበት እየተከታተሉት ነበርና ምንም ነፃነት አልተሰማውም። በአንድ ሳምንት የተመለሰበት ምክንያት ይህ ሲሆን ዋናው ቁም ነገር በዚያ ሳምንት ውስጥ በትግራይ ያገኘው ትምህርት ነበር። በዚያን ግዜ በትግራይ ውስጥ በያለበት የሚውለበለበው የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ሳይሆን የወያኔ አርማ ነበር። ነገር ግን በእያንዳንዱ ቤት በር ወይም ግድግዳ ላይ በትንንሹ ተቆርጦ የተለጠፈ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ነበር ብሎ ነገረኝ የትግራይ ተወላጆች "የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ አታስረሱንም!" እያለ ለወያኔ የሰጠው መልስ ነበር። ኢትዮጵያዊነትና ትግሬነት አይለያዩም፡ ፀሐይና ሙቀትዋም አይለያዩም።

የትግራይና የመረብ ምላሽ ተወላጆች የደም የቋንቋና የባሕልም፡ የታሪክም ዝምድና ያላቸውና አካባቢያቸውም ኢትዮጵያን የወለደ ማሕፀን እንደነበረ በድንጋይ ላይ ተፅፎ የቀረ የማያከራክር ሐቅ ነው። ሆኖም ወያኔና ሻዓቢያ ይህንን ክደው መረብ ምላሽን ከኢትዮጵያ ታሪክ አስወጥተው፡ የትግሬዎችና መረብ ምላሽ ተወላጆችን ዝምድና ሰርዘው ከዚያም አልፈው ባዕድና ጠላቶች አድርገው በክፉ ጦርነት ደም አቃብተዋቸዋል፡፡ ይህ ሆኖአል፡፡

ሌላ የቀረ የወያኔ ተልዕኮ ያለ ይመስላል። ይህም የትግራይን ተወላጆች ከቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለመለየትና ባዕድ አድርጎ ደም ለማቃባት ነው፡ እስካሁን አልተነካም፡፡ ምክንያቱም በአንድ በኩል አብዛኞቹ የትግራይ ተወላጆች በታሪክ፡ በባህልና በደም እንዲሁም በዜግነት የተሳሰሩበትን ሰንሰለት ጥንካሬ ስለተገነዘቡ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ የቀረው አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ የትግራይ ተወላጆችን ኢትዮጵያዊነትና ዝምድና ስለሚገነዘብ ነው። በትግራይ ተወላጆች መሃከል እንክርዳዶች እንዳሉ ሁሉ በቀረውም የኢትዮጵያ ሕዝብ መሃከል እንክርዳዶች አሉ። በሁለቱም በኩል መርዛቸውን የሚነዙት እንክርዳዶቹ ናቸው። የእነዚህን በሁለት በኩል በተለያዩ ጎራዎች የበቀሉ እንክርዳዶች መርዝ መቋቋም የመለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ግዴታ ነው።

አንዱ ይህንን ክፉ ችግር የመቋቋሙ መንገድ መርዙን በትክክል ማወቅ ነው። መርዙ ምንድን ነው? በመሰረቱ መርዙ ጥላቻ ነው፡ ጥላቻው ግን የተለያየ ነው። በአንድ በኩል በደረቅ ሥልጣን ጥም ምክንያት የአንድ አገር ሕዝብ በመከፋፈልና በጥላቻ በማጣመድ ኃይልን ለማጠናከርና ተቃውሞን ለማዳከም ሆን ተብሎና ታስቦበት የሚነዛ የጥላቻ መርዝ ነው። ይህ የአገዛዝ ሁሉ ባሕርይ ነው፡ በሕዝብ ፍላጎትና ፈቃድ በአብዛኛው ሕዝብ ተደግፎ የቆመ መንግሥት በሌለበት አገዛዝ ከፋፍለህ ግዛ በሚባለው እኩይ ዘዴ ይጠቀማል። በደርግ ዘመን መደብ ተብሎ ሃብታምና ድሃን ማጋጨት ነበር። ወያኔ ደግሞ የተለያዩ ቋንቋዎች ተናጋሪዎችን በማጋጨት በመሃል ወያኔ ራሱን በዙፋኑ ላይ ለማቆየት እየሞከረ ነው። ወያኔ ትግሬዎችን በሙሉ ወደራሱ ጎራ ለማስገባትና ለማሰለፍ ሲል የትግሬዎችን ትግሬነት ከአስፈላጊው

mesfinwoldemariam.org

mesfinwoldemariam.org

በላይ በማጉላትና ኢትዮጵያዊነታቸውን በማሳነስ በመሣሪያነት ሲስላቸው ከቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በታቀደ ቅራኔ ያጣምዳቸዋል። እንዲያውም የትግራይ ተወላጆች በሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የጥላቻ ኢላማ ሆነው የሚታዩ በማስመሰል ትግሬዎች በፍርሃትና በስጋት እንዲኖሩና ወያኔን እንደመከታና አለኝታ እንዲመለከቱ ከባድ ሙከራ እያደረገ እስከአሁን እየተውተረተረ ይገኛል።

ወያኔ በአገዛዝ ላይ በመሆኑ ለትግራይ ተወላጆች ወገናዊነት ያለው እያስመሰለ የትግራይ ተወላጆች ላይ የአብሪትና የማንአለብኝነት ስሜት እያነጸረ፥ በሌላ በኩል ደግሞ በጥቂቶች ሌሎች ላይ በወያኔና በትግሬዎች መሃከል ያለውን ድንበር እያጠፋ ለወያኔ ዓላማ የተመቸ ሁኔታን ይፈጥራል። በአጠቃላይ ሲታይ ከትግራይ ውጭና ከኢትዮጵያ ውጭ ባሉ አብዛኛው ትግሬዎች ላይ የወያኔ ዓላማ እንደከሸፈ የማያጠራጥር ነው። በትግራይ ክልል ውስጥ ግን ትግሬዎች በሃይል ተጠርንፈውና ታፍነው እውነተኛ ፍላጎታቸውንና ፈቃዳቸውን የሚገልጹበት ነፃነት በጭራሽ የለም። ሌላው ቢቀር ነፃነታቸውን በሙሉ ተገፍፈው በከፋ ጭቆና ውስጥ የሚኖሩ ትግሬዎች የጨቋኞቻቸውን ዓላማ ለማሳካት ይሰለፋሉ ብሎ ማመን ቂልነት ይሆናል። የወያኔ መርዝ በአንድ ወይም በሌላው መልኩ በትግራይ የሚኖሩትን አይነካም ማለትም ቂልነት ይሆናል። ቢያንስ በሌላው ሕዝብ ላይ እንዲያድርባቸው ወያኔ የሚነዛውን ጥላቻ ባይቀበሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ ይጠሏቹሃል እየተባለ የሚነዛባቸው መርዝ ጥርጣሬ፥ ፍርሃትና ስጋት ሳያሳድርባቸው አይቀርም። ለዚህም አንዳንድ ምልክቶችን በሌላ በኩል ያዩ ይሆናል።

ከላይ ለመግለጽ የተሞከረው ወያኔ በቀጥታ በትግራይ ተወላጆች ላይ የሚነዛውን መርዝ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በቀጥታ ሳይሆን በተዘዋዋሪ መንገድ በትግሬዎች ላይ የሚነዛ መርዝ አለ። ምንጩ ያው የወያኔ አገዛዝ ቢሆንም በሌላ በኩል ተላልፎ በትግራይ ተወላጆች ላይ የሚሰነዘር ነው። አንዳንድ ሰዎች በግንዛቤ ማነስም ይሁን በንዴትና በብስጭት የአእምሮ ሚዛናቸው ይበለሻል። ወያኔንና ትግሬን መለየት ያቅታቸውና ትግሬውን ሁሉ እንደወያኔ ወይም እንደውያኔ ደጋፊ፥ ወይም በወያኔ አገዛዝ እንደተጠቀመ አድርገው ይመለከታሉ። ስለዚህም በወያኔና በትግሬዎች መሃከል ያለውን ድንበር ማየት ይሳናቸዋል። ወያኔ ማለት ትግሬ፥ ትግሬ ማለት ወያኔ መስሎ ይታያቸዋል። ስለዚህም በትግሬዎች ባደረባቸው የጥላቻ መርዝ ሳያውቁት የወያኔን ዓላማ ያራምዳሉ፥ ንጹሑንና በኢትዮጲያዊነቱ የሚኮራውን ትግሬ ያሰደነብራሉ።

መርዙ ራሱና የሚሄድባቸውም አቅጣጫዎች በአጭሩም ቢሆን አሁን ግልጽ ሳይሆኑ አይቀርም ብዬ አምናለሁ። በሁለቱም አቅጣጫዎች የመጨረሻው የመርዙ ማረፊያ ትግሬዎች ናቸው ማለትም ከወያኔ በቀጥታ በትግሬዎች ላይ የሚረጨው መርዝና ከሌሎች በወያኔና በትግሬ መሃከል ያለውን ልዩነት የማያውቁ ሰዎችም በትግሬዎች ላይ የሚረጩት መርዝ ናቸው። ከየትም አቅጣጫ ቢመጣ መርዙ ጥላቻ ነው።

እዚህ ላይ ሁለት ነጥቦችን ማንሳት ያስፈልጋል። አንደኛው ጥላቻ ከጠላትነት ጋር የተያያዘ ነው። የጠላትነት ስሜት ደግሞ የሚገፋፋው ወደመጠፋፋት ነው። እንግዲህ ማን ነው የማን ጠላት የሚሆነው? ማንስ ነው ማንን አጥፍቶ የሚኖረው? አገሩ የጋራ ነው፥ አብሮ መኖርም ግዴታ ነው። በአንድ አገር ዜጎች መሃከል የሚኖረው የአመለካከትና የእምነት ልዩነት ወደጠላትነት አያመራም። የፖለቲካ እምነት ልዩነት ጠላትነት ሳይሆን ፉክክር ፤ ፉክክሩም ለአንድ አገርና ለአንድ ሕዝብ የተሻለ አመራርን ለመስጠት ነው። የተፎካካሪዎቹ ዓላማ አንድ ነው ፤ አገራቸውንና ሕዝባቸውን ወደላቀ የእድገት ደረጃ ለማድረስ ነው። እንዲህ ከሆነ ሕዝቡ ነፃነት ያለው የሥልጣን ባለቤት ሆኖ ከተፎካካሪዎቹ መሃከል ይበጀኛል የሚለውን የሚመርጥበት ሥርዓትን መፍጠርና በሕግ መገዛት ነው። ዴሞክራሲ የሚባለውም ይኸው ነው።

ሁለተኛው ነጥብ በኢትዮጵያ በአሁኑ ግዜ ከየአቅጣጫው የሚረጨው የጥላቻ መርዝ የፖለቲካ መሠረት የሌለው መሆኑ ነው። ፖለቲካ የእምነትና የአመለካከት ልዩነት በሰላማዊና ሕጋዊ ትግል መፍትሔን የሚያስገኝ የማኅበረሰባዊ ኑሮ ዘዴ ነው። ስለዚህም በእምነትና በአመለካከት ላይ ያለውን ልዩነት በውይይት በክርክር መለወጥና ማቀራረብ ይቻላል። በጎሣ ልዩነት ላይ ግን ሲከራከሩ ዕድሜን ቢፈጁም ምንም ዓይነት ለውጥ ማምጣት አይቻልም። የአንድ ጎሣ አባል የሆነ ሰው ከሌላ ጎሣ አባል ጋር ለመግባባት ሲል የጎሣውን መልክ ወይም መለያ ሊለውጥ አይችልም። መሆንን ሁሉም መቀበል አለበት። ሴት ወይም ወንድ መሆንን ከመቀበል ሌላ አማራጭ የለም፥ ሲከራከሩ ቢውሉ ሴትዋ ትንሽ ወደ ወንድነት ወንዱም ትንሽ ወደ ሴትነት አይጠጉም፥ በጎሣም በዘርም በሃይማኖትም ያው ነው። ልዩነትና ክርክር በሃሳብ ደረጃ እንጂ በመሆን ደረጃ ፍሬን አያስገኝም።

ስለዚህም ጎሣን ተንተርሶ የሚመጣ አድልዎም ሆነ ጥላቻ ከእንስሳ ደመ ነፍስ ስሜት እንጂ ከአእምሮ ካለውና ማሰብ ከሚችል ሰው አይደለም። የአንድ አገር ሕዝብ በዜግነታቸው በእኩልነት ስለሚቆሙ ሕጋዊ መብቶቻቸውና ግዴታዎቻቸው በምንም ምክንያት አይበላለጡም። አንድነታቸውም የቆመበት

መሠረት የጾታ ወይም የዕድሜ የጎሣ ወይም የዘር የቋንቋ ወይም የሃይማኖት ልዩነቶቻቸው ላይ ሳይሆን በዜግነት እኩልነታቸው ላይ ነው። ለዚህ ነው የውጭ ጠላት ሲመጣባቸው በአንድ ላይ ሆነው ማናቸውንም ከፍተኛ መስዋዕትነት የሚከፍሉት። አብሮ ለመሞት የተዘጋጀ ሕዝብ አብሮ ለመኖር አይቸግረውም። ለዚህ ነው የጥላቻውን መርዝ ከመካከላችን ነቅለን ማውጣት ያለብን ፤ ለዚህ ነው ትግሬነትን ከወያኔነት ጋር ማደባለቅ የሌለብን ፤ ለዚህ ነው ትግሬነት በኢትዮጵያዊነት ዜግነት የኢትዮጵያን ባለቤትነት ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር የመካፈል መብት ያለው ፤ ለዚህ ነው ትግሬነት ከኢትዮጵያዊነት የሚፈልቅ ጥላቻ አለ ብሎ መስጋትና መፍራት የሌለበት ፤ ለዚህ ነው ኢትዮጵያዊነት ለሚሰማው ዜጋ ሁሉ ወያኔ የሚለውን የፖለቲካ ቡድን ከትግሬነት ነጥሎ ማየት ግዴታው የሚሆነው።

ኢትዮጵያ የሁላችንም አገር ነች።  የሁላችንም ስል መካነ ልደት በሆነው በትግራይ የሚኖሩትንና ወያኔንም ይጨምራል። ወያኔ ሌላ ነገር የለውም፣ ወደደም ጠላም። ስለዚህም ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ተስማምቶና ተፋቅሮ ከመኖር በቀር ሌላ አማራጭ የለውም።

ኢትዮጵያዊነት ኢትዮጵያውያን በሙሉ ወያኔም ጭምር አብረው የሚጎናጸፉት ታሪካዊ የዜግነት ካባ ነው። መሬትዋም። የሁላችንም የኑሮ መሠረት፣ ካባውም የሁላችን ክብርና ኩራት ነው።

ዘመነ ግርምቢጥ ወይም የተገላቢጦሽ ዘመን እንዳይሆን ልናደርገው የምንችለው እኛው ነን። ልባችንን ከጥላቻ ካጸዳነው መልካም ዘመንን እንፈጥራለን። ጥላቻ ያፈርሳል እንጂ አይገነባም ፤ ያራርቃል እንጂ አያቀራርብም። የፉክክር ቤት ሳይዘጋ ያድራል የሚባለውም ሊያስተምረን ይገባል።

በመወያየትና በመከራከር የምንፈልገውንና የሚጠቅመንን ሥርዓት ለመፍጠር እያንዳንዳችን እንደዜጋ ወይም በፈለግነው ዓይነት ቡድን ውስጥ ብንሆንም ከሁላችንም በላይ ሊዳኘን የሚችል ትክክለኛ ሚዛን አለው ብለን የምናምንበት አስገዳጅ ኃይል እንዲኖር ያስፈልገናል።  በእግዚአብሔር ለምናምን እግዚአብሔርን ባለሚዛን እናደርጋለን።  ከዚያም ከወረደ ሕግ ሌላ ሚዛን ይሆነናል። ይሉኝታ ማለትም በሕዝብ እርስ በርሱ የሚያወራው ሚዛን ይሆናል።  በመጨረሻም አእምሮና ኅሊናችን የራሳቸው ሚዛን ይኖራቸዋል። ችግራችን ሁሉ የሚፈጠረው “ባለሚዛኑ እኔ ብቻ ነኝ ፤ እግዚአብሔር የለም ፤ ሕግ የለም ፤ አእምሮ የለም ፤ ይሉኝታ የለም ፤ ጡንቻ ብቻ ነው፣” ከሚሉ ሰዎችና ከጭፍሮቻቸው ነው። እንዴት እንንገራቸው? እንዴት ለማዳ እናድርጋቸው? እንዴት ብለን ከነሱ በላይ ባለሚዛን መኖሩን እናሳያቸው? እንዴት ብለን አገሩ የሁላችንም መሆኑን እናስገንዝባቸው?

ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ-ማርያም
ከቃሊቲ